በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

## በደብረ ዕንቍዕ ቅድስት ማርያም ወቅዱስ ሩፋኤል ገዳም

## በቤተክርስቲያን ዙሪያ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች ገንዘብ የማሰበሰብ ሥራን በሚመለከት የወጣ ደንብ

መግቢያ፡

በቤተክርስቲያን ዙሪያ ካሉ ምእመናንና ለጋሾች ገንዘብ በማሰባሰብ ለበጎ አድራጎትና ለቤተክርስቲያ ልማት ሥራዎች ማዋል በእጅጉ የተለመደ ተግባር መሆኑ ይታወቃል። በገዳማችንም ይሄው አሰራር የተለመደና ለረጅም ጊዜ ስንጠቀምበት የቆየን ሲሆን በዚህም ብዙ ገንቢ የልማትና የበጎ አድራጎት ስራዎች ተሰርተዋል። ነገር ግን በአንዳንድ አጋጣሚዎች ይህንን በጎ ልማድ ገንቢ ባልሆነና ግልጽነት በጎደለው መልኩ የመጠቀም አዝማሚያዎች እየታዩ መጥተዋል። ይህም ምእመኑን እንዲሁም የሰበካ አስተዳደር ጉባዔውን አላስፈላጊ ወደ ሆነ ውዝግብ ያስገባበት ሁኔታ መፈጠሩ ይታወሳል። ይህንን ውዝግብ ለመፍታት በሽምግልና የተቀመጡ ወንድሞች ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት አንድ ወጥ የሆነ ደንብ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን እንደ አንድ የመፍትሔ አቅጣጫ አድርገው አስቀምጠዋል።

በዚህም መሰረት የገዳሙ የሰበካ አስተዳደር ጉባዔ ገዳሙንና ምእመናኑን ከመሰል ህገወጥ ድርጊቶች ለመጠበቅ ይህንን ደንብ አውጥቷል።

1. ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባል በገዳሙ ውስጥ ካሉ ምእመናን ለማንኛውም ጉዳይ ገንዘብ ማሰባሰብ ቢፈልግ በቅድሚያ ጉዳዩን ለሰበካ አስተዳደር ጉባዔው በጽሁፍ አቅርቦ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።
2. ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባል በገዳሙ ውስጥ ካሉ ምእመናንም ሆነ ባለንበት አካባቢ ከሚገኙ ለጋሾቻችን በገዳማችንም ሆነ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስም ገንዘብ ማሰባሰብ ቢፈልግ ጉዳዩን ለሰበካ አስተዳደር ጉባዔው በጽሁፍ አቅርቦ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።
3. ገንዘብ የሚሰባሰበው በኢትዮጵያ ላለ ደብር፤ ገዳም ወይም የአብነት ት/ቤት የሆነ እንደሆነ ጠያቂው አካል ተረጅው ተቋም ከሚገኝበት ሃገረ ስብከት የተጻፈ ሕጋዊ የእርዳታ መጠየቂያ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል።
4. የሰበካ አስተዳደር ጉባዔው ለሚቀርቡለት የገንዘብ ማሰባሰብ ጥያቄዎች ከአራት ሳምንታት ባልበለጠ ጊዜ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል።
5. የሰበካ አስተዳደር ጉባዔው ገንዘብ እንዲሰበሰብ ፈቃድ የሚሰጥ ከሆነ፤ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል የገዳሙ ማህተም ያለበትን የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እንደዚሁም እንደአስፈላጊነቱ የውክልና ደብዳቤ አዘጋጅቶ ገንዘቡን ለሚሰበስበው አካል ይሰጣል።
6. ገንዘቡን የሚሰበስበው አካል በደረሰኝ ገንዘቡን ካሰባሰበ በኋላ ደረሰኙንና የተሰበሰበውን ገንዘብ ለገዳሙ ሂሳብ ክፍል ገቢ ያደርጋል።
7. የገዳሙ የሒሳብ ሰራተኛ ገንዘቡን ወደ ቤተክርስቲያን አካውንት ገቢ ያደርጋል።
8. የተሰበሰበው ገንዘብ ለገዳሙ ልማት የሚውል ከሆን፤ በገዳሙ የሂሳብ አሰራር መሰረት እየወጣ ለተሰበሰበለት አላማ እንዲውል ይደረጋል።
9. የተሰበሰበው ገንዘብ ለሶስተኛ ወገን የሚተላለፍ ከሆነ፤ ገቢ የተደረገው ገንዘብ ከቤተክርስቲያን በቼክ ገንዘቡን ላሰባሰበው አካል የሚከፈል ሲሆን፤ ይሄው ቼኩን የተቀበለው አካል ከሶስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ገንዘቡ ለታቀደለት አላማ መዋሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ለሰበካ አስተዳደር ጉባዔው ማቅረብ ይኖርበታል።

የደንቡ ተፈጻሚነት፤

ይህ ደንብ ለገዳሙ ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀብሮ የገዳሙ መተዳደሪያ ደንብ አካል በመሆን በሁሉም የገዳሙ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ሕዳር **2016** ዓ ም